# አረምን በእንክርዳድ!

## የሞቀው የአትላንታ እንቅስቃሴና ህፀፁ

**ከተስፋሁን**

የጃንዋሪ ወር በአትላንታ አካባቢ ተወካዩች ያሏቸው የፖለቲካ ደርጅቶች ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደረጉበት ወቅት ነበር። ጃንዋሪ 11 2007 “Peace on Trial in Ethiopia” በሚል ርዕስ በተካሄደ ኮንፈረንስ ከአሜሪካውያን ጋር ሰፊ ውይይት ተደርጓል። ከዚያም ጃንዋሪ 13 2007 በህብረቱ ድጋፍ ኮሚቴ አዘጋጅነት በወቅታዊ ሁኔታወች ላይ ያተኮረ የኢትዮጵያዉያን ውይይት ተደርጓል፤ በዚሁ ቀን የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር መስራች የኢንጂነር ቅጣው አመታዊ የሙት መታሰቢያ በኢብአግ ተዘጋጅቷል። ጃንዋሪ 14 2007 በዶክተር ሞገስ የሚመራው የቅንጅት ክፍል፣ ጃንዋሪ 20 2007 በሻለቃ ዮሴፍ የሚመራው የቅንጅት ክፍል የውስጥ ችግራቸውን በተመለከተ መንስኤውንና ውሳኔዎቹን ለህዝብ ለማሳወቅ ስብሰባዎችን አድርገዋል፤ ጃንዋሪ 15 2007 የታላቁ ማርቲን ሉተር ኪንግ መታሰቢያ ሰልፍ አዘጋጅ ኮሚቴ በጠራው ሰላማዊ ሰልፍ የኢትዮጵያዉያን ተሳትፎ እና ሌሎች መሰል እንቅስቃሴዎች በአትላንታ ከተማ ሲጧጧፉ ሰንብተው ነበር።

በእውነቱ ይህን ዓይነት ንቅናቄ እየተዳከመ የመጣውን የትግል እንቅስቃሴ እንደገና ህይወት ለመዝራትና ወደነበረበት ግለቱ ለማሸጋገር የበኩሉን አስተዋፅኦ ይኖረዋል የሚል እምነት ቢኖረኝም በእንቅስቃሴው ወቅት የነበሩትን ህፀፆች በአግባቡና በወቅቱ ማረም ካልታቻለ ደግሞ ወደ ሌላ ፅንፍ በመሄድ በልዩነቶች ላይ ውጥረት ጨምሮ ወደ ደንቃራነት ስለሚለወጥ በአየኋቸው ክስተቶች ላይ የግል አስተያየቴን እንድሰጥ ህሊናዬ አስገደደኝ።

ጃንዋሪ 11 2007 “Peace on Trial in Ethiopia” በሚል ርዕስ የአንድ ቀን ኮንፈረንስ የተካሄደው የታላቁ ማርቲን ሉተር ኪንግ ልደት ጋር በተያያዘ በሚከበረው የአንድ ሳምንት ባዕል ውስጥ አፍሪካን አሜሪካዉያን አንዱን ቀን በሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ላይ ኮንፈረንስ አዘጋጅቶ የመወያየት ልምድ የቆየ ስለነበር በዚህ አመት ይችን ቀን በአፍሪካ የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ላይ በተለይም በኢትዮጵያ ዙሪያ ውይይት እንዲካሄድ የዜጎች መብት ታጋዮች (Civil Right Leaders) እና ሰብአዊ መብት ተከራካሪዎች ፍላጎት በማሳየታቸው በኦጋዴን ህዝብ የሰብዓዊ መብት ታጋዮች ዋነኛነትና በሌሎችም የኢትዮጵያ ድርጅቶች ተባባሪነት ዝግጅት ተቀነባብሮ የአንድ ቀን ሙሉ ኮንፈረንስ ተደርጎ ነበር።

በዚህ ኮንፈረንስ የተለያዩ ልምዶች ያሏቸው በተለያዩ የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ Civil Right Leaders እና የሰብዓዊ መብት ተከራካሪዎች ተገኝተዋል። ምንም እንኳን ጥቂት ነጮች ቢኖሩም ብዙዎቹ አፍሪካን አሜሪካውያን ናቸው። ከአፍሪካ የመጡ ጥቂት የመንግስታት ባለስልጣናትም ተገኝተው ነበር። በዝግጅቱ የመጀመሪያ ክፍል በኢትዮጵያ ያለዉን የሰብዓዊ መብት ጉዳይ ፓለቲካዊ ያልሆኑ ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ከማቅረባቸው በፊት ታላላቅ የሰብዓዊ መብት መሪዎችና Civil Right Leaders አጨጭር ንግግር እንዲያደርጉ ተጋብዘው ነበር። ተጋባዦቹ ከታሪክ አንፃር ስለኢትዮጵያ በቂ ግንዛቤ ያላቸው በመሆናቸው ጥሩ ጥሩ ነገሮችን አንስተው ነበር። በእርግጥ በቆየዉና ባለው የዉስጥ ችግሮች ላይ ብዙ ባያተኩሩም ህዝባችን ለነፃነት ያለውን ቀናኢነትና ጀግንነት አመስግነዋል። ኢትዮጵያ ለጥቁር ህዝቦች ያላትን ተምሳሌነትና ታሪካዊነትም አስምረውበታል። ይህንንም የበለጠ ፍሬያማ ለማድረግና አሁን ያሉብንን ችግሮች ለማስወገድ ደጋግመው ደጋግመው ከልዩነታችን ይልቅ በአንድነታችን ላይ እንድናተኩርና መከፋፈል ችግሩን እንደሚያባብሰ እንጂ መፍትሄ አለመሆኑን አስረግጠው መክረውንም አስተምረውንም መድረኩን ለባለጉዳዮች አስረከቡ።

ከዚህ በኋላ ከታናጋሪዎቹ ውስጥ አንድዋ የኦጋዴን ሰብዓዊ መብትን በተመለከተ ያቀረቡት ወ/ሮ ፎዝያ የወከሉትን ክፍል መሰረት በማድረግ አጠር ያለ ዝግጅት ይዘው ቀረቡ። ወይዘሮዋ የኦጋዴንን ህዝብ ችግር እንደ አንድ የኢትዮጵያ ችግር አድርገው ሲያቀርቡ የዚህ ክፍል የኢትዮጵያ ህዝብ በሶስት ታሪካዊ ወቅቶች ለየት ያለ በደል ደርሶበታል በማለት ማብራሪያቸውን በጣፈጠ አቀራረብ ካቀረቡ በኋላ አሁን ባለው ሁኔታም ይህ ህዝብ ለከፍተኛ አደጋ ተጋልጠ ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰበት መሆኑን ሲያስረዱ በተለይ ደግሞ የአቶ መለስ መንግስት በሱማሌ ጉዳይ ከሚያደርገው ጣልቃ መግባት ጋር በተነካካ የኦጋዴን ህዝብ መብትና ደህንነት ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጠ መሆኑን በሚያሳምኑ መረጃዎች አስደግፈው ካሳዩ በኋላ ኢትዮጵያውያን የውስጥ ችግራችንን ለመፍታት በግልፅና በእኩልነት የምንሰራበትን መንገድ መያዝ እንዳለብን ጠቁመው ለዚህም በኢትዮጵያዊነታቸው የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንደሚያደርጉ ቃል ገብተው ተሰናብተው ወጥተዋል።

ከወ/ሮ ሶፍያ በኋላ እድሉ ከተሰጣቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ የኦሮሞ ድጋፍ ቡድን ተወካይ ዶክተር መሐመድ ያቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠው በኦሮምኛ ተናጋሪው ህዝብ ላይ የሚፈጸመውን በደል ይሁን እንጂ ችግሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የተዛባና ኢ-ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ አንፃር ሲያቀርቡት ይህ ችግር በሌሎቹም የኢትዮጵያ ክልሎች እየተፈፀመ መሆኑን በማያያዝ በመግለፃቸው አቀራረባቸው ምሁራዊ ችሎታን የሚያሳይ ነበር። ዝግጅታቸውም በተሰጠው አጀንዳ ዙሪያ ያተኮረ ስለነበር "The Arrogancy of Political Power" War in the name of democracy" በሚሉ ትንተናወች ላይ ያቀረቡት ሃሳብ የመጡበትን ተልእኮ በደንብ እንዲወጡ አድርጓል። ሌላው ዝግጅት ደግሞ የኦሮሞ ጥናት ማህበር (Oromo Study Association) ተወካይ ለሆኑት የለዶክተር አሰፋ ጃለታ ነበር። ዶክተሩ ሰፋ ያለ ዝግጅት ያደርጉ ይመስለኛል። "Duality of Ethiopianism የሚሉትን ፍልስፍናቸውን መሰረት በማድረግ ገና ወደ መድረክ እንደወጡ "የወደፊቱን ለመነጋገር ያለፈ ታሪካችንን መቃኘትና በዚያ ዙሪያ ላይ መተማመን ያስፈልጋል" ካሉ በኋላ ከዚህ በፊት በኦሮሞ ህዝብ ላይ ተፈፀም ያሉትን በደል ማስረዳት ሲሞክሩ "ሴሚቲክ አማራዎችና ትግሬዎች ኩሾቹን ኦሮሞዎች ባሪያ (Slave) አድርገው ሲጠቀሙባቸው ሲሸጡና ሲያሸጡዋቸው ለረጅም ዘመናት የቆዮ ዘረኞች ናቸው" ካሉ በኋላ ለአሜሪካውያኖቹ ሰፋ አድርገው ሲያብራሩ "እናንተ ዘረኝነትን የምታዩት በነጭና በጥቁር ማህል የነበረውን ግንኙነት ነው በኛ ክልል ግን ዘረኞቹ አማራዎችና ትግሬዎች እዚህ ነጮች እንዳደረጓችሁ ሰብዕናችንን ገፈው slave ብለው ሸጡን ረዥም ዘመን ግፍ ተፈፀመብን" እያሉ የጥቁር አሜሪካውያንን ስሜት በሚኮረኩር አቀራረብ ሰፊ ዲስኩር ሲያደርጉ ኢትዮጵያዊውን ቀርቶ በአዳራሹ ውስጥ ያሉትን ሌሎች ዜጎችን በሚያስቀጣ መልክ ፀረ ኢትዮጵያ ቅስቀሳቸውን ሲገፉ ጊዜያቸውን ጨረሱ። አንዳንድ ሰዎች ግለሰቡ የመጡበትን አጀንዳ አያውቁትም ነበር ወይ እያሉ ሲጠይቁ በመልካቸው የየመን አረቦችን የሚመስሉት ዶክተር አሰፋ እራሳቸውን የኩሽ ዘር ወራሽ ሌላውን (ከሳቸው የተሻለ የኩሽ ደም ያለውን) የሴሜቲክ ዘር ማለታቸው ቤታቸው ውስጥ መስታዋት ባይኖር ይሆን የሚል ጥያቄ አስነስቷል። በዶክተሩ የቀረበው "የEthiopian racism እና Ethiopian Christian Empire Ideology" ትንተና አስደንጋጭ ነበር።

ከዶክተር አሰፋ ቀጥሎ የቀረቡት ዶክተር መቅደስ መስፍን ነበሩ። የዶክተር መቅደስ አቀራረብ ግልፅ፣ አድማጭን የሚስብና ጥርት ያለ የቋንቋ አቀራረብ የነበረው ስለነበር ጥሩ ነበር። ሆኖም የሳቸው ትኩረት በቃሊቲ ላይ ብቻ ያነጣጠረ ከመሆኑም በላይ ብዙውን ጊዜ ያባታቸውን ንግግር በመጥቀስና በማብራራት ላይ ያመዘነ ስለነበር የጥናታዊ ፅሁፋቸውን አድማስና የጉዳዩን ስፋት አጥብቦታል። ሌላው ተናጋሪ የአኝዋኩ ተዋላጅ አቶ ኡባንግ መድረኩን ሲይዙ ቀዝቅዞ የነበረው አዳራሽ እንደሞቀ ተሰማኝ የአቶ ኡባንግ የንግግር ችሎታና የሚያቀርቡት ቁም ነገር አዳራሹ

ውስጥ የነበረውን አድማጭ በቀላሉ ለመቆጣጠር አስችሎቸው ነበር። በኢትዮጵያዊነቴ እኮራለሁ የሚሉት አቶ ኡባንግ በአኝዋክ ህዝብ ላይ መንግስት ጭፍጨፋ ሲያካሂድ ጭፍጨፋውን ለማስቆምና ለሌላውም የአለም ህብረተሰብ ለማሳወቅ ጥረት ሲያደርጉ አድማጭ አጥተው እንደነበርና ይህን ችግር ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ከተወጡ በኋላ ወደቦታው በመሄድ መረጃዎቹን እንዴት እንዳቀናበሩ ከገለፁ በኋላ በኢትዮጵያ በተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ ጊዜያት እንደዚህ አይነት ጭፍጨፋዎች የሚፈፅመው የኢህአዴግ አምባገነን መንግስት መሆኑን አስረድተዋል። በሌላ በኩል አቶ ኡባንግ ከዚህ በፊት ከነበሩት ተናጋሪዎች ውስጥ አንዳቸው ያለአግባብ ወጥረውት የነበረውን ልዩነት በመጠኑ ሲያረግቡት የቆየ ታሪክ (እዉነትነት ያለውንና የፈጠራም) ላተኮረ ልዩነትን ከማስፋት ይልቅ አንድ የሚያደርጉንን ሃሳቦች እያጠናከርን በመተባበርና በአንድነት መብታችንን ለማስከበር መስራትና መታገል ይመረጣል በማለት አሳሰበዋል።

ከአቶ ኡባንግ በኋላ እጃቸውን በሰንሰለት በማሰር መደረኩን የያዙት አቶ ክፍሌ ሙላት በኢትዮጵያ ነፃው ፕሬስ የጋጠመዉን ችግርና በጋዜጠኞች ላይ የሚፈፅሙትን ግፍ ሃገራችን የገጠማትን ችግር በሰፊው በማተት የኢትዮጵያውያንን የነፃነትና የዴሞክራሲ ጥማት ለማስረዳት ሞክረዋል። የክፍል አንዱ ዝግጅት ከመጠናቀቁ በፊት ክ Civil Rights እና ከHuman Rights ታጋይ ጥቁር አሜሪካዉያንና ከአፍሪካ የመጡ ተወካዮች አጫጭር ንግግሮች አድርገው ነበር፤ እነኝህ እንግዶች በንግግራቸው ዉስጥ የታዘቡትን ጉድለቶቻችንን እና ድክመቶቻችንን ጠቁመው ነበር። ብዙዎቹ በንግግራቸው ዉስጥ "በአለፉ ችግሮች" ላይ ከማተኮር ይልቅ አሁን በተጨባጭ ባለው ችግር ላይ ትኩረት በመስጠት በአንድነት እስካልታገልን ድረስ የውጭ ድጋፍ (በተለይ ከአፍሪካዉያንና ከጥቁር አሜሪካዉያን) ማግኘት እንደማንችል አስረግጠው በመናገር በትግላችን ውስጥ ማስታካከል ያለብን ነገር እንዳለም ምክራቸውን ገልፀዋል። ከዚህ በኋላ በጊዜ እጥረት ምክንያት የጥያቄና መልስ ክፍለ ጊዜው ሳይንዛዛ እረፍት ተደርጎ ወደሁለተኛው ክፍል ውይይት ተገባ።

የኮንፈረንሱ ሁለተኛ ክፍል ከፖለቲካው ትግል አንፃር የፖለቲካ ድርጅቶች ያለውን ችግር ለማስወገድ ያላቸውን የመፍትሔ ሃሳብ የሚያቀርቡበት ነበር። በዚህም መሰረት የመጀመሪያው ታናጋሪ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጭ ግንባር (ONLF) ተወካይ አቶ መሐሙድ ነበሩ። የአቶ መሐሙድ አቀራረብ ግልፅ አልነበረም፤ በእርሳቸው አባባል "ወደ ኋላ ተመልሰን ታሪክን ማየት አለብን" በማለት የጀመሩትን ንግግር ሲቀጥሉ ሙሉ ጊዜውን ዳግማዊ ምኒልክና ንግስት ቪክቶርያ ተፃፃፉ የሚሉትን ደብዳቤዎች በማንበብ የተሰጣቸው ጊዜ አለቀ። ምንም እንኳን በሳቸው አባባል ኦጋዴን የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት እንደሆነች ተደርጎ ቢገለፅም አሁን ያለውን ችግር ለማስወገድ ጠቃሚ መፍትሔ ለማቅረብ ቀርቶ የድርጅታቸውን የትግል አቅጣጫ ማቅረብ ሳይችሉ የመድረኩ መሪ ደጋገሞ በሰጣቸው ማስጠንቀቂይ ወደ ወንበራቸው ተመለሱ። ተመሳሳይ አመለካከትና አደረጃጀት ያላቸው ተናጋሪ የነበሩት የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር OLF ተወካይ ዶክተር ኑሮ ናቸው። ዶክተሩም እንደ ቀደምቱ ተናጋሪ "ወደ ኋላ መለስ ብለን ታሪክን ካላየን የወደፊቱን መነጋገር አንችልም" በማለት የኦሮሞ ህዝብ ታሪክ ከኢትዮጵያ ጋር ሲያቀርቡ፤ የኦሮሞ ህዝብ በኢትዮጵያ ኢምፓየር ቅኝ ተገዝቶ የቆየና አሁን በዚያው መንገድ እየኖር እንደሆን በመግለጽ ትግላቸውም ለኦሮሞ ህዝብና ለኦሮሚያ ነፃ መውጣት መሆኑን ካሳዩ በኋላ በቅርቡ በተደረገው ድርድር የተመሰረተዉን "ትብብር ለነፃነትና ዴሞክራሲ" (AFD) እንዲፈጠር ኦነግ (OLF) ከፍተኛ ጥረት አድርጎ ድርጅቶቹን ለማሰባሰብ የተጫወተውን ሚና ገልፀው ከአሁን በኋላ ኢሕአዴግን ለማስወገድ የሚፈልጉ ድርጅቶች በሙሉ "አስፈላጊውን ፎርማሊቲ" በማሟላት በአባልነት ለመመዝገብ እንደሚፈቀድላቸው ገልፀዋል። የኦነግ (OLF) ተወካይ ይህንን ንግግር ሲያደርጉ ለብዙወቹ (በተለይም AFD አባላትና ደጋፊወች) አስደንጋጭ ነበር። በኦነግ (OLF) አካባቢ የአመለካከት ለውጦች ተደርገዋል እየተባለ ሲቀሰቀስ ከቆየ በኋላ አጋጣሚ ሲገኝ ተመልሶ

ወደነበረበት የተዛባ አቋም ሲገፋ በተለይ ደግሞ ይህ በአመራር ደረጃ ባሉት ሰዎች መታየቱ ትልቅ ቅሬታ ፈጥሯል። ይሄም ከዚህ በፊት ባንዳንድ የኦነግ (OLF) አባላት የታየውን የመለስለስና የመቀራረብ ስሜት የሚሰብር በመሆኑ የሚደረጉትን ጥረቶች የሚያበላሽ፣ የቆየዉን የጥርጣሬ ስሜት የሚያዳብር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የቅንጅቱ ተወካይ ዶክተር አብርሃምና የኅብረቱ ተወካይ ዶክተር ስዩም በተከታታይ ወደ መድረኩ በመቅረብ ስለድርጅቶቻቸው ራዕይ በመግለፅ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ፍትሃዊና ደሞክራሲያዊ ያልሆነ አስተዳደር አስወግዶ የሁሉም ህዝብ መብት የሚከበርባት ደሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለመገንባት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ትብብር እንደሚያስፈልግ ቢጠቅሱም ከዚህ በፊት ቀርበው የነበሩትን አክራሪና የተዛቡ አቀራረቦች ለማስተካከል ብዙም ሙከራ አላደረጉም። ዶክተር አብርሃም በንግግራቸው ላይ ከፍተኛ ትኩረት የሰጡት የቅንጅቱን ድልና የመሪዎቹን መታሰር መሰረት አድርገው ሲሆን ዶክተር ስዩም ደግሞ የኅብራቱን ኅብረ ብሔራዊነት በመግለፅ የኢትዮጵያን ችግር ለመፍታት ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት የሚያካትት ሰፊ የሕዝብ መሰረትና ድጋፍ ያለው የፖለቲካ ንቅናቄ ካልተደረገ ይህ በጠመንጃው የሚተማመን መንግስት ሥልጣኑን ሊለቅ እንደማይችል ገለፀው ሁሉም ድርጅቶች በዚህ ላይ እንዲያተኩሩ የውጪም አለም በተለይ ደግሞ አፍሪካ አሜሪካዉያን ለዚህ አይነት ተልእኮ ድጋፋቸውን እንዲሰጡ ጠይቀዋል።

የቀኑ ስብሰባ ካለቀ በኋላ ሁሉም ሃይሎች በተገኙበት የራት ግብዣ ተደርጎ ነበር። በዚህም ወቅት በዝግጅቱ የተሳተፉ የአካባቢው ተወካዮች አጠር አጠር ያሉ መገለጫ እንዲሰጡ በዝግጅቱ መሪ በአቶ ያሲን በመጋበዛቸው የኦጋዴኑ ተወካይ በኦጋዴን ሕዝብ በደል ላይ ያተኮረ ገለፃ ሲያደርጉ የኦነግ ተወካይ ደግሞ በማናቸውም ድርደር ከድርጅቱ ፖሊሲ ውጭ ፍንክች እንደማይሉ ሲያብራሩ የሕብረቱ ተወካይ ደግሞ ሕብረ ብሔር በመሆናችን በሃገራችን ሉዓላዊነት ላይ ጠንካራ አቋም ስለአለን የኦሮሞ ሕዝብ ችግር አይመለከታችሁም፣ በአማራ ጉዳይ መግባት አትችሉም፣ የትግሬ ተወካይ እኛ ብቻ ነን . . . ወዘተ የሚሉት በብሔር ላይ የተደራጁ ድርጅቶች አመለካከት ስህተት መሆኑን ገለፀው ኅብረ ብሔር ድርጅቶች የሁሉም ህዝብ የሁሉም ብሔር/ብሔረሰብ ችግር ችግራቸው ጥያቄው ጥያቄያቸው መሆኑን ሲያብራሩ ከዚያም አልፎ የአማራው ችግር የኦሮሞ፣ የኦሮሞው ችግር የትግሬው፣ የትግሬው ችግር የአፋሩ . . . የሌላውም የሌላውም ነው። በኢትዮጵያዊነታችን ያንዱ ችግር ያንዱ ነው። በዳያችንና የምንታገለው አንድ ኢ-ዴሞክራቲክ ስርዓት ነው። በማለት ሲያብራሩ የአርበኞች ግንባርን ወክለው ሲሳተፉ የቆዩት ደግሞ “መጀመሪያ ወያኔን እንጣልና ከዚያ በኋላ ምን አይነት አስተዳደርና ስርዓት እንመስርት የሚለዉን እንወያያለን” የሚለውን በኦነግ ሰዎች የተሰነዘረውን አመለካከት በመቃወም መጀመሪይ ምን አይነት አስተዳደርና ስርዓት እንገነባለን በሚለው ስንተማመን የታጠቁና ያልታጠቁ ኃይሎችን አሰልፈን በዚህ መልክ መስማማት አደገኛ ስለሆነ ቀዳሚ መሆን ያለበት በምንገነባው ስርዓት ላይ መስማማቱ ነው በማለት ያላቸውን ስጋት ገለፀው ነበር። ሌሎችን ተወካዮች ተጋባዦችንና ጋባዦቻቸውን በማመስገን አጠር አጠር ያለ ንግግር ያደረጉ ሲሆን አሁንም ጥቁር አሜሪካዉያኑ የተሰጣቸውን እድል በመጠቀም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ኃይል በመተባበር በኢትዮጵያዊነት ኮርቶ መብቱን ለማስከበር እንዲታገል ምክራቸውን ሲለግሱ ይህ ሁኔታ ሲፈጠር እነሱም ከጎናችን ቁመው በድፍረት አጋራችን መሆን እንደሚችሉ እየገለፁ በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተከፋፈልን ከሆነ ግን ብዙ እንደሚቸገሩ ገለፀዋል። ብዚሁ ሳምንት ሌላው አትላንታ የተከናወነው አብይ ጉዳይ በኅብረቱ ድጋፍ ኮሚቴ የተጠራው ህዝባዊ ስብሰባ ነበር። በዚህ ስብሰባ በአካባቢው ለሚንቀሳቀሱት የፖለቲካና የሲቭክ ድርጅቶች በሙሉ በቀጥታ እንዲሳተፉ በደብዳቤ ተጋብዘው አላማዉም በወቅታዊ የሃገራችን ጉዳይ ላይ እንዲሁም የፖለቲካና የሀሊና እሥረኞችን በተመለከተ ከተወያዩ በኋላ አንዳንድ ስራዎችን በጋራ ለመስራት ታስቦ ስለነበር ለሁሉም ድርጅቶች የግብዣ ደብደቤ ቢላክላቸውም አርበኞች ግንባር በተወካዮች ችግር፣ ኦነግ በስራ ብዛት መገኘት እንደማይችሉ ሲገልፁ የቅንጅት ተወካዮች ግን እንደተለመደው ምንም መልስ ባለመስጠት ካለመሳተፋቸውም

በላይ እንዳቸውም በስብሰባው ላይ ሳይገኙ ቀርተዋል። የዚህ ስብሰባ አንዱ አላማ በክርስትና እና በእስልምና አማኝ ኢትዮጵያዉያን መሃል ያለው ግንኙነት በአንዳንድ አካባቢ የተፈጠሩት ክስተቶች እንዳያበላሹት ሁለቱን ወንድማማች ኢትዮጵያዉያን የህዝብ ክፍሎች ለማስገንዘብ ታስቦ ስለነበር የሁለቱም ሃይማኖቶች ተወካዮች ተገኝተው ሰፊ ትምህርት በመስጠት ኢትዮጵያዊ አንድነታችን ለማጠናከር የሚጠቅም ስራ ተሰርተዋል። በአዳራሹም በታየው ፊልም በኢትዮጵያ የክርስትና እና እስልምና ግንኙነት የተጀመረው በሰላማዊ መንገድ በመሆኑ ለረጅም ጊዜ ያለምንም ችግር እንደቆየ ሁሉ ወደፊትም በመከባበር አብረው እንደሚኖሩ ማሳየት ተችሏል። በዚህ ስብሰባ ሁለት የኅብረቱ ስራ አስፈፃሚ አባላት (ዶክተር ሰዩምና አቶ ኡባንግ) ከምሁራን ዶክተር ወርቁ ከአገር ወዳድ አቶ ተፈሪ በየተራ ወደ መድረኩ በመምጣት ለሃገርና ለወገን የሚጠቅም ሰፊ ትምህርት ሰጥተዋል። የዚህ ሰሞን ሌላው አስደሳች ስራ በጃንዋሪ 15 2007 የታላቁ የማርቲን ሉተር ኪንግን ልደት ምክንያት በማድረግ በየአመቱ በሚካሄደው የሰላማዊ ሰልፍ ላይ ኢትዮጵያውያን ያደርጉት እንቅስቃሴ ነው። በዚህ ሰልፍ በርካታ ኢትዮጵያዉያን ባንዲራቸውን በመያዝ በሰልፉ ጎልተው በመታየት ከአፍሪካ አሜሪካዉያን ጋር ያላቸውን አጋርነት ማሳየት ብቻ ሳይሆን በዕለቱ ከነበሩት ተናጋሪዎች ዉስጥ ሁለቱ ከአፍሪካውያን (የጋና እና የኢትዮጵያ) ለሕዝቡ ንግግር የማድረግ እድል አግኝተው ነበር። የኢትዮጵያውያን ተወካይ አቶ ኡባንግ ሜቶ ነበሩ። አቶ ኡባንግም ኢትዮጵያዉያን ለአፍሪካ አሜሪካዉያን ታጋዮች ያላቸውን አክብሮት ከገለፁ በኋላ ሃገራችን ለዴሞክራሲና ለሰዎች ልጆች መብት መከበር በምታደርገው ትግል አፍሪካን አሜሪካዉያኑ ከጎናችን እንዲቆሙ አሳስበዋል። አቶ ኡባንግ ንግግር ለማድረግ ሲወጡ አቶ ክፍሌ ሙላት በሃገራችን የነፃ ጋዜጠኞችን ሰቆቃ፣ መፃፍና መናገር የሚያስከትለውን ችግር ለማንፀባረቅ እጃቸውን በሰንሰለት ታስረው ለህዝብ ይታዮ ነበር። በርካታ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ባንዲራቸውን በማውለብለብ እየዞሩ፤ ሁሉም የፖለቲካና የሕሊና እስረኞች እንዲፈቱ የሚጠይቁ መፈክሮችን በመያዝ ልዩ በሆነ መልክ የሚያኮራ ስራ ሲሰሩ ውለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ ወር በአንድ ሳምንት ውስጥ በአትላንታ ከተማ ሁለቱም የቅንጅት ቡድኖች መሪወች በመሃከላቸው የተፈጠረውን ችግር ህዝብ እንዲያውቅ በሚል ሁለት ስብሰባወች ጠርተዋል። በመጀመሪያ (እሁድ) በዶክተር ሞገስ የሚመራው የቅንጅቱ ቡድን በውስጣቸው የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት የተደረጉትን ሙከራዎች፤ ሙከራዎቹን ማን እንዳከሸፈ እንዲሁም ብዙ ተዛማጅ ነገሮችን በማንሳት በእሳቸው ቡድን እይታ ያለውን በስብሰባው ለተገኙት ኢትዮጵያውያን ለማስረዳት ሞክረዋል። በቀጣዩ ሌላ ስብሰባ ደግሞ በሻለቃ ዩሴፍ የሚመራው ዶክተር አልማዝንና ሌሎችንም ያቀፈው ቡድን የችግራቸውን መንስኤ፣ ችግሩን ለማስወገድ ያደረጉትን ጥረትና የወሰዱትን እርምጃ፣ ችግሩ እንዲባባስ ያደረጉትን ሁኔታዎችና ግለሰቦችን በመዘርዘር ከነሱ አቋም አንፃር ህዝብ ማወቅ አለበት የሚሉትን ለማስረዳት ሞክረዋል። በሁለቱም ስብሰባዎች እንደወትሮው ሰው በርከት ብሎ አለመምጣቱ የህዝቡን ስሜት የሚነኩ ነገሮች እየተፈጠሩ መሆናቸውን ጠቋሚ ይመስለኛል። በስብሰባው ጊዜ በሁለቱም ወቅት ህዝብ ለማሳመን ሲባል አላስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች እየተነሱ ለጠላት ጆሮ መድረሳቸው አሳዛኝ ነው። ቢያንስ እስር ቤት የተጣሉት ሰዎች እስኪወጡ እራሳችንን መቆጣጠር ለምን ያቅተናል? በቅራኔ አያያዝና አፈታት ላይ ብዙ ፖለቲከኞችንና ድርጅቶቻቸው ተደጋጋሚ ስህተት ሲሰሩ ይታያሉ። ቡድናዊነት ከብሔራዊ ጥቅም በላይ ሁኖ እኔ ያልኩት ካልሆነ ገደል ይግባ፣ የኔ ወንበር ካልተመቻቸ ይበተን በሚሉ አሳፋሪ የግለሰቦች ባህሪዎች ብዙ ድርጅቶች የደረሱባቸው ችግሮች ስናይ እጅግ ያሚያሳዝን ነው።

እንግዲህ ፅሁፌን ወደ መደምደሙ ስደርስ አንዳንድ ነጥቦችን አፅንኦት ሰጥቼ ባልፍ የሚመረጥ ይመስለኛል። በአትላንታ አካባቢ የሚንቀሳቀሱት ኢትዮጵያዉያን ድርጅቶች በአጠቃላይ ከአፍሪካን አሜሪካዉያን ጋር በተለይ ደግሞ ከCivil Rights እና Human Rights እንቅስቃሴ መሪዎች

ጋር የጀመሩት ግንኙነትና ስራ ይበል የሚያሰኝ በጎ ልምድ ስለሆነ በአርአያነቱ በሌሎቹም ቦታዎች ብንጠቀምበት በጣም ጠቃሚ ነው። ወደ ኋላ ታሪካችንን ብንመረመር በዚህ ዙሪያ ብዙም ስራ አልሰራንም ግንኙነታችንም ደካማ ነው። ከአሁን በኋላ ይህን የህዝብ ክፍል እና የትግል እንቅስቃሴ ኢትዮጵያዉያን ከምናደርገው ትግል ጋር ማቆራኘቱ የሁሉም ኢትዮጵያውያንና ድርጅቶች የስራ ክፍል ቢሆን ጥሩ ነው። በእንቅስቃሴው ወቅት የነበሩት ህፀፆች ደግሞ ካልታረሙ አደገኞች ናቸው። በኮንፈረሱ ቅንጅቶች በAFD ከኦነግ ጋር ባላቸው ትስስር ለOLF ስፊና የተደጋገመ መድረክ ለመስጠት ምቹ ነበሩ። ኅብረቱ የነበረው ዕድልና ድምፅ ጠባብ በመሆኑ ሂደቱን ማቆም ስለማይችል በማኩረፍ ከመድረኩ ከመራቅ ይልቅ በአገኛት መድረክ የሚችለዉን ማድረጉ ትክክል ነበር። በዶክተር አሰፋ ትንተና ብዙ ሰዎች (ኦሮሞዎቹንም ጨምሮ) እንዳልተከሰቱ ማወቅ ተችሏል። ንግግራቸው እንደጠበቁት የጥቁር አሜሪካውያንን ስሜት መንካት አልቻለም። በእሳቸው ሙከራ መነቀል ያለበትን ጭቆና (አረም) በመንቀል አደገኛ አመለካከታቸውን (እንክርዳድን) መዝራት አልቻለም። መቸም ዶክተር ናቸውና ለምን ደፈርከኝ ካላሉን በቀር ዶ/ር አሰፋ የሰሜኑን ክፍል አማራና ትግሬ ብለው በሴሜቲክ ጎራ ሲያጠቃልሉት የደቡብ ክፍል ኦሮሞ አድርገው በኩሽነት ሲፈርጁት ከምን የሰው ስነፍጥረት ታሪክ መረጃ (Anthropological Facts) ላይ ተነስተው እንደሆነ ለማወቅ ይቸግራል። ይህንን ተረት ተረት ከዚህ በፊት እንደሚሉት ከቤተ መንግስት ተጠግተውና ታዘው ታሪክ ከፃፉ ሰዎች ወርሰው ከሆነ ደግሞ የሚያተዛዝብ ነው። እነዚህ በዶክተር አሰፋ የተነሱት "የሴሜቲካዊነትና የኩሻዊነት" ልዩነቶች ወይም በዶክተር ኑሮ የተነሱት "የቀኝ መገዛት ታሪክ" ኦሮምኛ ተናጋሪው ሕዝብ ለሙብቱ መከበር የሚያደርገዉን ትግል አቅጣጫ የሚያስት ብቻ ሳይሆን የፊውዳሉ ስርአትና ባህል በሕዝቡ ላይ ያደረሰው በደል እንዳይታይ የሚጋርድ ነው። በኢትዮጵያ የነበሩት የዘውድ ገዥዎች ቢያንስ የመጨረሻወቹ ሶስቱ የሰለሞን (አይሁዳ) ዘር የሚል ተቀጥላ ታሪክ በመጨረሻው ንጉስ ፈቃደኝነት ይፃፍላቸው እንጂ በውስጣቸው የነበረውን የተከበረ የኦሮሞነት የጉራጌነት ደም ማንም በሰሪንጅ ስቦ ሊያስወግደው የሚችል ጉዳይ አይደለም።

በአሁኑ ወቅት ብዙ ድርጅቶች ከዚህ በፊት ከነበሩዋቸው አመለካከቶች ወጥተው በመቀራረብ የህዝብ መብት ማስከበር የሚችል ኃይል ሊመሰርቱ ነው እየተባለ በሰፊው ሲቀሰቀስ ይሰማል። በዚህ ወር በአትላንታ ከታየው ልምድ ግን ብዙም ተስፋ የሚሰጥ አይደለም።።በዚህ አይነት ተማምኖ ቤተ መንግስት መግባት ይቅርና ተመሳሳይ አቋም አለን ብሎ ወደ መድረክ መምጣት አደገኛ መሆኑን የ AFD ቤተሰቦች ሊያስቡበት ይገባል። ድርጅቶችን ማረምና ማስተካከል የሚቻለው ቤተ መንግስት ገብተው የሰማዩን አየር የምድሩን ታንክ የሚጠቀሙበትን ጉልበት ከሰጠናቸው በኋላ ሳይሆን ከዚያ በፊት ነው። የህዝብን ፍላጎትና የህሕዝብን ድምፅ የማይቀበል ድርጅት፣ በህዝባችን አብሮ መኖር ላይ መርዝ የሚረጭ ድርጅት፣ ህዝባች በእኩልነት ተከባብሮ እንዲኖር ከልቡ ያልተቀበለ ድርጅት ነገ እድል ቢያገኝ የህዝብ መብት ያከብራል የሚል እምነት መጣል አይቻልም። ስለዚህ ትግላችን አረም ነቅሎ እንክርዳድ ለማብቀል መሆን የለበትም። ስንዴ ለማምረት እንጂ ህዝብን የማይከፋፍል መልካም አስተዳደር የህዝበ እኩልነት የሚረጋገጥበት የህግ የበላይነት የሚታይበት ስርአት ለመገንባት እንጂ አንዱን አምባጋነን በሌላ አምባገነ ለመተካት መሆን የለበትም።